# የመድረኩ መመስረት - መልካም ዜና ነዉ !

ግርማ ካሣ ( muziky68@yahoo.com)

ሰኔ 27 2008

የቀድሞ የኢትዮጵያ ፕሬዘዳንት ዶ/ር ነጋዶ ጊዳዳንና በኢሕአዴግ ከስድት አመት በላይ የታሰሩት የቀድሞ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሚኒስቴር አቶ ስዬ አብርሃን ጨምሮ የተወሰኑ የፖለቲካ ድርጅቶች "መድረክ ለዲሞክራሲና ምክክር በኢትዮጵያ " የሚል የጋራ የመነጋገሪያ መድረክ አቋቁመዋል። ይህ መድረክ በሰኔ 17 2000 ባወጣዉ መግለጫዉ የጠቀሳቸዉ፣ ጥያቄ ሊፈጥሩ የሚችሉ አንዳንድ አባባሎች አሉ። [1]

- ለምሳሌ "በሀገሪቱ የፌዴራል ስርዓትን የሚደነግገዉ ሕጋዊ ማዕቀፍ እንደተጠበቀ ሆኖ" የሚለዉ አባባል አንዱ ነዉ። በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ዉስጥ ያሉና በሕጋዊነት እየሰሩ ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ሕገ መንግስቱን አክብረዉ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች መሆናቸዉ ይታወቃል። አሁን ያለዉን የፌደራል አሰራር ይቀበላሉ። ነገር ግን በሕገ መንግስቱ መሰረት አሁን ያለዉን በዘርና በቋንቋ ላይ ብቻ የተመሰረተዉን የፌደራል አሰራር ለመለወጥ የሚፈልጉ፣ «ፌዴራሊዝሙ ዘርን ብቻ ሳይሆን ጂኦግራፊን፣ ኢኮኖሚን እንዲሁም የሕዝቡን ፍላጎት አመለካከት ዉስጥ የከተተ ፌደራሊዝም መሆን አለበት» የሚሉ ወገኖች በርካቶች ናቸዉ። ታዲያ ይህ መግለጫ "አሁን ያለዉን የፌደራል ስርዓት የሚደነግገዉ ሕጋዊ ማእቀፍ እንደተጠበቀ ሆኖ" ብሎ ሲያስቀምጥ በሕገ መንግስታዊ መንገድ የፌዴራሊዝሙ አይነት መቀየር አለበት የሚሉትን ኃይላት የሚያገል ሊሆን ይችላል ብዬ አስባለሁ።

- በሁለተኛ ደረጃ ይህ መግለጫ የግሰሰብ፣ የብሄር፣ የቡድን የመሳሰሉ መብቶች በተጓዳኝ መከበር እንዳለባቸዉ ያሰምራል። ነገር ግን እነዚህ መብቶች እርስ በርስ ቢጋጩ የትኛዉ መብት ቅድሚያ ሊሰጠዉ እንደሚገባ አያስረዳም። «ከሁሉም በላይ የግለሰብ መብት ቅድሚያ ሊሰጠዉ ይገባል፤ የብሄርም ሆነ የቡድን መብት የግለስብ መብትን ባልነካ መልኩ ነዉ መጠበቅ ያለበት» ብለዉ የሚከራከሩ አሁንም ብዙ ናቸዉ። ለምሳሌ በአንድ አካባቢ የብሄር መብት ነዉ ተብሎ በሽሪያ መሰል ሕግ መተዳደር አለብን ብለዉ ዜጎች ቢነሱና በሴቶች ላይ አፋኝ እንቅስቃሴዎች ቢፈጸሙ ለብሄሩ መብት ነዉ ቅድሚ የሚሰጠዉ ወይንስ ለሴቶች መብት ? በመግለጫዉ ሁሉንም መብቶች በአንድ መስመር ማሰፈሩ ትንሽ የጠራ አቋምን ከመያዝ አንጻር ከወዲሁ ችግር ያለበት ይመስለኛል።

- መግለጫዉ «የኢትዮጵያ ሕዝብ» ከማለት ይልቅ «የኢትዮጵያ ሕዝቦች» የሚል አባባል መጠቀሙ በአንዳንዶቻችን ዘንድ ጥያቄ ፈጥሯል። ይህ አባባል ብዙም የከፋ ችግር ባይኖረዉም የኢትዮጵያዉያንን አንድነት ሳይሆን መከፋፈል አጉልቶ የሚያሳይ አባባል ስለሆነ ብዙም የሚወደድ አይመስለኝም። አሮሞዉ፣ ትግሬዉ፣ ጉራጌው፣ ከንባታዉ፣ ድብልቁ ...ሁሉም ኢትዮጵያዊ ነዉ።ሁላችንም በጋራ አንድ ሕዝብ ነን። ልዩነቶች ይኖሩናል። ነገር ግን ልዩነታችን የዉበታችን ምልክት ነዉ።፡እንደ ተለያዩ ህዝቦች አድርጎ ሊያሳየን የሚገባ አይመስለኝም። ይሄን ብዬ ግን "የኢትዮጵያ ሕዝቦች" እያሉ የሚጠሩትን ግን እንደዚያ የማለት መብታቸዉ ሙሉ ለሙሉ የተጠበቀ እንደሆነ ሳልዘነጋ ነዉ።

ከላይ እንደዘረዘርኩት አንዳንድ ጥያቄዎችን መድረኩ በአንዳንዶቻችን አይምሮ ዉስጥ የፈጠረ ቢሆንም፣ የዚህ መድረክ መመስረት በጣም በከፍተኛ ደስታ ነዉ የተቀበልኩት። አንድ ተብሎ ነዉ ወደ ሁለት፣ ከዚያም ሶስት ... ከዚያም ወደ መቶ የሚደረሰዉ።

- **ኢትዮጵያዉያን በአንድ ላይ ሆነዉ መነጋገርና መመካከር መቻላቸዉ እራሱ በጣም የሚያስደስትና ሊበረታታ የሚገባዉ ትልቅ ድል ነዉ።** ኢትዮጵያዉያን የጎደለንና ያጣነዉ ነገር ቢኖር ቁጭ ብሎ መመካከርና መነጋገር ነበር። ችግሮቻችን ቢቻል በጥያት ካልተቻለም ደግሞ በስድብ መፍታት እንጂ በስለጠነ ፖለቲካና በሰላም ልዩነቶችን መፍታት ብዙም አልለመደብንም።

  ታዲያ እነዚህ ድርጅቶች ዉስጥ ዉስጡን ሲነጋገሩ ቆይተዉ በጋራ ለመስራትና በዜጎቿ እኩነት ላይ የተመሰረተች አንዲት ኢትዮጵያን ለመገንባት መወሰናቸዉን የሚያበስር መግልጫ ሲያወጡ ኢትዮጵያዉያንን በሙሉ በጣም ደስ

---

[1] http://www.ethiopiazare.com/images/doc/pdf/pr/2008/080622_medrek_pr.pdf

የሚያሰኝ ዜና ነዉ እላለሁኝ።

- ሌላዉ ያስደሰተኛ ቁም ነገር ቢኖር ይህ መድረክ ኢትዮጵያ ዉስጥ የተመሰረተ መድረክ መሆኑ ነዉ። ለነጻነትና ለዲሞራሲ የሚደረገዉ ትግል ፍሬ ሊያፈራ የሚችለዉ የትግሉ ማዕከል ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ  በሚኖርበት በኢትዮጵያ ዉስጥ ሲሆን ብቻ ነዉ። ትግል ከዉጭ አገር በኢሜል ወይንም ከአስመራ በሚተላለፍ ሬዲዮ ጣቢያ ሊመራ አይችልም። ዋናዉ ትግል ኢትዮጵያ ዉስጥ ነዉ መደረግ ያለበት። ሕዝብን ከዉጭ ሆኖ እያዘዙ ሳይሆን ሕዝብ በራሱ ተነሳሽነት ሞተር ሆኖ ትግሉን እንዲያንቀሳቅስ ሲደረግ ነዉ ዉጤቱ ሊመጣ የሚችለዉ።

- በሶስተኛ ደረጃ የዚህ መድረክ መመስረት ያስደሰተኝ በሰለጠነ ፖለቲካና በሰላማዊ ትግል የሚያምኑ ድርጅቶች መድረክ መሆኑ ነዉ። አገራችን ኢትዮጵያ ባዶ የዘራፍ ፖለቲካ በሚያራምዱ ስትታመስ ቆይታለች።፡ችግራችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየበዛና እየሰፋ ነዉ እንጂ የመጣዉ የተሻለ ነገር አልታየም። እንደገና ጦርነት እንደገና እልቂት እንደገና መገዳደል የሚበጀን ነገር አይደለም። ይህ ባህል አንድ ቦታ መቆም መቻል አለበት። ስለዚህም የመድረኩ የሰላም አቋም በጣል አስደስቶኛል።

- ይህ መድረግ ሊያስፈጽማቸዉ ያቀዳቸዉ አንገብጋቢ ነጥቦች የኢትዮጵያን ሕዝብ ትረታ የያዙም ነጥቦች ይገኙበታል። የኢትዮጵያን አንድነት ሊያረጋግጡ ፈቃደኛ እንዳልነበሩት አንዳንድ ትብብሮች ይህ መድረክ በማያሻማና በማያደናግር ሁኔታ የኢትዮጵያን አንድነትና ሉዓላዊነት ያረጋገጠ መድረክ ነዉ። እዚህ መድረክ ውስጥ በአጋዴን የሚኖሩ ኢትዮጵያን መካከል የሚንቀሳቀስ የሱማሌ ሕዝብ ዲሞካሲያዊ ቅንጅት፣ በምርጫ ዘጠና ሰባት ከ አሥራ አንዱ መቀመጫዎች ዘጠኙን በምዕራብ ወለጋ (የኦነግ ደጋፊዎች አሉበት የሚባለዉ አካባቢ)  ያሸነፈዉና በዶ/ር ቡልቻ ደመቅሳ የሚመራዉ የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ፣ የቀድሞ አንጋፋ የሕወሃት አመራር አባላትን የያዘዉ የትግራይ አሬናና የኢትዮጵያ ሕዝብ ዲሞራሲያኢ ኃይሎች ሕብረት ይገኙበታል። እነዚህ ሁሉ ድርጅቶች "ኢትዮጵያ አንድ ናት" ነዉ ብለዉ የተነሱት። ይህም ሌላዉ ሊያስደስት የሚገባ ነገር ነዉ እላለሁኝ።

- በአምስትኛ ደረጃ እነዚህ ከተለያዩ የአገራችን ክፍሎች የተወጣጡ ድርጅቶች አንድ ላይ መምጣታቸዉ ኢሕአዴግንም ጨምሮ ለሌሎች ድርጅቶች ፈር ቀዳጅና መልካም አጋጣሚን የሚሰጥ ነዉ። ዶ/ር ቡልቻ ደምቅሳ መድረኩ ኢህአዴግንም የሚጋብዝ እንጂ ያገለለ መድረክ እንዳልሆነ አስረድተዋል። የኢሕአደግ መንግስትም በማስታወቂያ ሚኒስቴር በኩል በለቀቀዉ መግለጫ የዚህን መድረክ መመስረት በአዎንታዊነት ተመልክቶታል። የዚህን መድረክ መመስረት የኢትዮጵያ ቴሌቭዥንን ያበሰረዉ ሲሆን ኢሕአዴግ ዉስጥ ያሉ ልብና አይምሮ ያላቸዉ ሰዎች አይለዉ እየወጡ እንደሆነ የሚያሳይ ሳይሆን አይቀርም።

በዚህ አጋጣሚ በአገር ቤት ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች የዚህ መድረክ ተሳታፊ ቢሆኑ የበለጠ መልካም ሊሆን እንደሚችል አስባለሁኝ። ልዩነቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ነገር ግን አሁን፣ ነገም ተነገ ወዲያም ለኢትዮጵያ መፍትሄዉ እኛ ኢትዮጵያዉያን ችግራች በንግግር ስንፈታ ብቻ ነዉ፡ ይህም ደግም ኢሕአዴግንም ይጨምራል።

በዉጭ አገር የሚንቀሳቀሱና የትጥቅ ትግል እናደርጋለን የሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶች  (የትጥቅ ትግል ገና ልንጀመር ነዉ የሚሉትንም ጨምሮ) በኢትዮጵያ ያለዉን ነባራዊ ሁኔታና እያራመዱት ያለዉ የጠመንጃ ትግል ለአመታት ለዉጥ እንዳላመጣ ተረድተዉ ከስሜታና በእልህ ፖለቲካ በነጻ መልኩ፣ የሚበጀዉንና የሚጠቀመዉን በኢትዮጵያ ሕዝብ ጉልበት ላይ የተመረኮዘዉን የሰለጠነ ሰላማዊ ትግል እንዲያራምዱ፣ እንዲሁም የዚህም መድረክ አባላትም ሆነው የሚንቀሳቀሱበትን መንገድ እንዲያመቻቹ  እመክራለሁኝ።

በጋራ በአንድነት የማይፈነቀል ድንጋይ የለም። ኢትዮጵያዉያን ከተባበርን በእጃችን ያለ ኃይል አለ። እጅ ለእጅ ከተያያዝን ለማየት የምንፈልጋትን ኢትዮጵያ በቅርብ ጊዜ እናያታለን።

እግዚአብሔር ሁላችሁንም ያክብርልኝ !
ኢትዮጵያ አገራችንንም ይባርካት !